# ቃል

# ሥጋ

# ሆነ

የሊጎኔር የነገረ ክርስቶስ

የእምነት መግለጫ

# ቃል ሥጋ ሆነ

የሊጎኔር የነገረ ክርስቶስ
የእምነት መግለጫ

Ligonier Ministries

The Word Made Flesh: The Ligonier Statement on Christology
Copyright © 2016 by Ligonier Ministries
Second edition
Published by Ligonier Ministries
421 Ligonier Court, Sanford, FL 32771
Ligonier.org | ChristologyStatement.com
Scripture quotations are from the ESV® Bible (The Holy Bible, English Standard Version®), copyright © 2001 by Crossway, a publishing ministry of Good News Publishers. Used by permission. All rights reserved.

ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው? አብዛኛው ሰው ስለ ኢየሱስ የራሱ የሆነ አመለካከት አለው። እነዚህ አመለካከቶች ጥልቀት የሌላቸው፣ ልክ ያልሆኑ፣ ወይም ጨርሶ መናፍቃዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ኢየሱስን በተመለከተ ያለው እውነት ግን፣ ተራ ምልከታ ብቻ ሳይሆን፣ ዘላለማዊ ፋይዳ ያለው ወሳኝ ጉዳይ ነው።

ክርስቲያን የሚለውን ስም የያዙ ሁሉ ክርስቶስን እንደ ደቀ መዛሙርቱ እንደሚከተሉ ይናገራሉ። ስለ ክርስቶስ ያላቸውን እይታ የሚያንጸባርቅ ነገረ ክርስቶስ፣ ማለትም አስተምህሮተ ክርስቶስ አላቸው። ይህ የነገረ ክርስቶስ አስተምህሮ፣ በተዘዋዋሪ ወይም በግልጽ የተብራራ ሊሆን ይችላል። የቅዱሳት መጻሕፍትን ጥልቅ መገለጥና መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ታሪካዊውን የክርስትና ግንዛቤ የሚወክል ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ አዲስና ከእግዚአብሔር ቃል ጋራ ግንኙነት የሌለው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ማንም ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው የነገረ ክርስቶስ ዕሳቤ የሌለው ሊሆን አይችልም።

ክርስቶስን መከተል የክርስትና ማዕከላዊ ጉዳይ በመሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያን በምናባችን የፈጠርነው ክርስቶስን ሳይሆን ታሪካዊውንና የቅዱሳት መጻሕፍቱን ክርስቶስን ለመስበክ ለዘመናት ደክማለች። የኒቂያ የእምነት መግለጫ (*Nicene Creed*)፣ የኬልቄዶን ጉባኤ (*Definition of Chalcedon*)፣ የሄድልበርግ የእምነት ማስተማሪያ (*Heidelberg Catechism*) እና የዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫን (*Westminster Confession*) በመሳሰሉ ታሪካዊ የእምነት መግለጫዎች፣ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ ያላቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት አብራርተዋል።

ዛሬ ላይ፣ እነዚህ መግለጫዎች ብዙውን ጊዜ ቸል ተብለዋል፤ ሰዎችም በተሳሳተ መንገድ ይረዷቸዋል። ይህም ሁኔታ የክርስቶስ ማንነትና ሥራን በተመለከተ በስፋት ግራ መጋባት እንዲፈጠር አድርጓል። ለክርስቶስ ክብርና ለሕዝቡ መታነጽ፣ ይህ የሊጎኔር የነገረ ክርስቶስ መግለጫ ታሪካዊውን፣ ትክክለኛውንና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ነገረ ክርስቶስን ጠቅለል አድርጎ ለመግለጽ ይፈልጋል። ይህንም የሚያደርገው ለመመስከር ቀላል በሆነ፣ የቤተ ክርስቲያንን ቋሚ እምነት ለማስተማር በሚጠቅምና ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የተውጣጡ አማኞች ለተልእኮ ዑብረው የሚሰባሰቡበት አንድ የጋራ መግለጫ ሆኖ ማገልገል በሚችል መልኩ ነው። ይህ መግለጫ የቤተ ክርስቲያንን ታሪካዊ የእምነት አንቀጾችንና መግለጫዎችን የሚተካ ሳይሆን፣ በክርስቶስ ማንነትና በሥራው ዙሪያ ያላቸውን የጋራ ትምህርት የሚያብራራ ማሟያ ነው። ክርስቶስ ለመንግሥቱ ይጠቀምበት።

*አር.ሲ. ስፕሮል፣ 2016 እ.ኤ.አ.*

በሥጋ በተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ፣ ነቢያችን፣ ካህናችንና
ንጉሣችን በሆነው ስም፣
የእግዚአብሔርን ሰው መሆን ምስጢርነትና አስደናቂነትን
እንመሰክራለን፤
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በተደረገልን ታላቅ
ድነትም ደስ ይለናል።

ከአብ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ፣
ወልድ ሁሉን ፈጥሯል፣
ሁሉን ደግፎ ይይዛል፣
ሁሉንም አዲስ ያደርጋል።
እውነተኛ አምላክ የሆነው እርሱ፣
በአንድ አካል ሁለት ባሕርያትን በመያዝ
እውነተኛ ሰው ሆነ።

ከድንግል ማርያም ተወለደ፣
በመካከላችንም ኖረ።
ተሰቀለ፣ ሞተ፣ ተቀበረም፤
በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሣ፤
ወደ ሰማይ ዐረገ፣
በክብርና በሁሉም ላይ ሊፈርድ
ተመልሶ ይመጣል።

ስለ እኛ፣
ሕግን ጠበቀ፣
የኀጢአታችን ማስተስረያ ሆነ፤
የእግዚአብሔርንም ቍጣ አረካ።
የመርገም ጨርቃችንን ወሰደ፣
የጽድቅ ልብሱንም ሰጠን።

እርሱ ነቢያችን፣ ካህናችንና ንጉሣችን ነው፤
ቤተ ክርስቲያኑን ይገነባል፤
ስለ እኛ ይማልዳል፤
በሁሉም ላይ ይነግሣል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው፤
ቅዱስ ስሙን ለዘላለም እንባርካለን።

አሜን።

# የምናምናቸውና የማናምናቸው አስተምህሮዎች

ከቅዱሳት መጻሕፍት
ማስረጃዎች ጋራ

**አንቀጽ 1**

ኢየሱስ በታሪክ ውስጥ ሰው ሆኖ የተገለጠ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ልጅና የሥላሴ ሁለተኛ አካል መሆኑን እናምናለን። እርሱ፣ እግዚአብሔር እንደሚመጣ የተናገረለት የተስፋው መሲሕ መሆኑንም እናምናለን።[1]

ኢየሱስ ክርስቶስ ተራ ሰው ወይም በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረ ልብ ወለድ ነው ብለን አናምንም።

**አንቀጽ 2**

በመለኮት አካላት አንድነት ውስጥ፣ ከዘላለም የተወለደው ወልድ ከአብ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ ዐይነት ባሕርይ *(consubstantial/ homoousios)* ያለው፣ እኩል የሆነና ዐብሮ ዘላለማዊ መሆኑን እናምናለን።[2]

ወልድ እግዚአብሔርን የሚመስል *(homoiousios)* ብቻ ወይም የማደጎ ልጅ ሆኖ በአብ ተቀባይነትን ያገኘ ሰው ነው ብለን አናምንም። በተጨማሪም፣ ወልድ ለዘላለም በባሕርይ ከአብ ያንሳል *(eternal subordination)* ብለን አናምንም።

**አንቀጽ 3**

ከኒቂያና ከኬልቄዶን የእምነት መግለጫዎች ጋራ በመስማማት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው፣ ለዘላለምም ሁለት ባሕርያት ያሉት አንድ አካል *(person)* መሆኑን እናምናለን።[3]

ወልድ ፍጡር ነው ብለን አናምንም። ወልድ መለኮት ያልነበረበት ጊዜ ነበር ብለን አናምንም። በተጨማሪም፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰብአዊ አካልና ነፍስ፣ ወልድ በታሪክ ውስጥ ሥጋ ከመሆኑ በፊት ነበሩ ብለን አናምንም።

---

1 በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋራ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። . . .ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም ዐደረ፤ እኛም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጅን ክብር አየን (ዮሐንስ 1፥1፣ 14)። በተጨማሪም፣ መዝሙር 110፥1፤ ማቴዎስ 3፥17፤ 8፥29፤ 16፥16፤ ማርቆስ 1፥1፣ 11፤ 15፥39፤ ሉቃስ 22፥70፤ ዮሐንስ 4፥25–26፤ ሐዋርያት 5፥42፤ 9፥22፤ ገላትያ 4፥4፤ ፊልጵስዩስ 2፥6፤ ቈላስይስ 2፥9፤ ዕብራውያን 5፥7፤ 1 ዮሐንስ 5፥20ን ይመልከቱ።

2 ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው (ማቴዎስ 28፥19)። በተጨማሪም፣ ዮሐንስ 1፥18፤ 3፥16–18፤ 10፥30፤ 20፥28፤ 2 ቆሮንቶስ 13፥14፤ ኤፌሶን 2፥18ን ይመልከቱ።

3 የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በርሱ ይኖራልና (ቈላስይስ 2፥9)። በተጨማሪ፣ ሉቃስ 1፥35፤ ዮሐንስ 10፥30፤ ሮሜ 9፥5፤ 1 ጢሞቴዎስ 3፥16፤ 1 ጴጥሮስ 3፥18ን ይመልከቱ።

**አንቀጽ 4**

የኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት ያለ መቀላቀል፣ ያለ መደባለቅ፣ ያለ መከፋፈል፣ ወይም ያለ መነጣጠል በአንድ አካል ውስጥ በአንድነት መሆናቸውን *(hypostatic union)* እናምናለን።[4]

በሁለቱ ባሕርያት መካከል ያለውን ልዩነት መግለጽ ማለት መነጣጠል ነው ብለን አናምንም።

**አንቀጽ 5**

ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ሲሆን፣ መለኮታዊና ሰብአዊ ባሕርያቱ የራሳቸውን መገለጫዎች *(attributes)* ይዘው እንደ ቀጠሉ እናምናለን። የሁለቱም ባሕርያት መገለጫዎች የአንዱ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል መገለጫዎች መሆናቸውን እናምናለን።[5]

የኢየሱስ ክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ መለኮታዊ መገለጫዎች አሉት፤ ወይም መለኮታዊውን ባሕርይን መያዝ ይችላል ብለን አናምንም። መለኮታዊው ባሕርይ መለኮታዊ መገለጫዎችን ለሰብአዊው ባሕርይ ያጋራል ብለን አናምንም። ወልድ ሰው ሲሆን ማንኛውንም መለኮታዊ መገለጫዎቹን ወደ ጐን ተወ ወይም አሳልፎ ሰጠ ብለን አናምንም።

**አንቀጽ 6**

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚታየው የእግዚአብሔር አምሳል፣ የእውነተኛ ሰውነት መለኪያና በመጨረሻም በመቤዠታችን ወደ እርሱ መልክ የምንለወጥ መሆኑን እናምናለን።[6]

ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሚመስል እንጂ የሚያስብ ሰዋዊ ነፍስ የሌለው ከእውነተኛ ሰው ያነሰ ነበር ብለን አናምንም። ወልድ ሰው ሲሆን የሰውን ባሕርይ *(human nature)* እንጂ የሰውን ማንነትና አካል *(human person)* ወስዷል ብለን አናምንም።

---

4 ስምዖን ጴጥሮስም፣ "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" በማለት መለሰ። ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ምስጉን ነህ፤ ይህን የገለጠልህ በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም አይደለም። (ማቴዎስ 16፥16−17)። በተጨማሪም፣ ሉቃስ 1፥35፣ 43፤ ዮሐንስ 1፥1−3፤ 8፥58፤ 17፥5፤ ሐዋርያት 20፥28፤ ሮሜ 1፥3፤ 9፥5፤ 2 ቆሮንቶስ 8፥9፤ ቈላስይስ 2፥9፤ 1 ጢሞቴዎስ 3፥16፤ 1 ጴጥሮስ 3፥18፤ ራእይ 1፥8፣ 17፤ 22፥13ን ይመልከቱ።

5 በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተም ዘንድ ይሁን፤ እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋራ መተካከልን ሊለቀቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ራሱን ባዶ አደረገ (ፊልጵስዩስ 2፥5−7)። በተጨማሪም፣ ማቴዎስ 9፥10፤ 16፥16፤ 19፥28፤ ዮሐንስ 1፥1፤ 11፥27፣ 35፤ 20፥28፤ ሮሜ 1፥3−4፤ 9፥5፤ ኤፌሶን 1፥20−22፤ ቈላስይስ 1፥16−17፤ 2፥9−10፤ 1 ጢሞቴዎስ 3፥16፤ ዕብራውያን 1፥3፣ 8−9፤ 1 ጴጥሮስ 3፥18፤ 2 ጴጥሮስ 1፥1ን ይመልከቱ።

6 እርሱ የማይታየው አምላክ አምሳል ነው፤ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ ነገር በርሱ ተፈጥሯል፤ በሰማይና በምድር ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ኀይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በርሱና ለርሱ ተፈጥሯል (ቈላስይስ 1፥15−16)። በተጨማሪም፣ ሮሜ 8፥29፤ 2 ቆሮንቶስ 4፥4−6፤ ኤፌሶን 4፥20−24፤ ዕብራውያን 1፥3−4ን ይመልከቱ።

አንቀጽ 7

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እውነተኛ ሰው፣ ዝቅ በማለቱ ወቅት የሰው ባሕርይ ተፈጥሮአዊ ውስንነቶችንና የተለመዱ ድክመቶችን ሁሉ እንደ ያዘ እናምናለን። ከኀጢአት ውጪ፣ በነገር ሁሉ እንደ እኛ መሆኑን እናምናለን።[7]

ኢየሱስ ክርስቶስ ኀጢአት አድርጓል ብለን አናምንም። ኢየሱስ ክርስቶስ መከራን፣ ፈተናን ወይም ችግርን በእውነት አልተቀበለም ብለን አናምንም። ኀጢአት የእውነተኛ ሰውነት መገለጫ ነው፤ ወይም የኢየሱስ ክርስቶስ ኀጢአት አልባ መሆን፣ እውነተኛ ሰው ከመሆኑ ጋራ ይቃረናል ብለን አናምንም።

አንቀጽ 8

ታሪካዊው ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል፣ በተአምራት ተፀንሶ ከድንግል ማርያም እንደ ተወለደ እናምናለን። ከኬልቄዶን የእምነት መግለጫ ጋራ በመስማማት፣ እርሷ የወለደችው ልጅ በሥጋ የተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅና የሥላሴ ሁለተኛ አካል በመሆኑ፣ እርሷ በእውነት "የአምላክ እናት" *(theotokos)* ተብላ መጠራቷ ትክክል መሆኑን እናምናለን።[8]

ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ባሕርይውንና ኀጢአት አልቦነቱ ከማርያም ያገኘው ነው ብለን አናምንም።

---

7 ስለዚህ በሁሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው፤ ይህንም ያደረገው መሓሪና ታማኝ ሊቀ ካህናት ሆኖ፣ እግዚአብሔርን ለማገልገልና ለሕዝቡ የኀጢአትን ስርየት ለማስገኘት ነው (ዕብራውያን 2፥17–18)። በተጨማሪም፣ ሚክያስ 5፥2፤ ሉቃስ 2፥52፤ ሮሜ 8፥3፤ ገላትያ 4፥4፤ ፊልጵስዩስ 2፥5–8፤ ዕብራውያን 4፥15ን ይመልከቱ።

8 በስድስተኛው ወር፣ እግዚአብሔር መልአኩ ገብርኤልን በገሊላ ወደምትገኘው ናዝሬት ወደምትባል ከተማ ላከው፤ የተላከውም ከዳዊት ዘር ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ነበር፤ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ (ሉቃስ 1፥26–27)። በተጨማሪም፣ ማቴዎስ 1፥23፤ 2፥11፤ ሉቃስ 1፥31፣ 35፣ 43፤ ሮሜ 1፥3፤ ገላትያ 4፥4ን ይመልከቱ።

አንቀጽ 9

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የመጀመሪያው አዳም በወደቀበት ነገር ሁሉ የተሰጠውን ተልእኮ በድል የተወጣና የክርስቶስ አካል ለሆነው ለሕዝቡ ራስ የሆነ የመጨረሻው አዳም መሆኑን እናምናለን።[9]

ኢየሱስ ክርስቶስ የወደቀውን የሰው ባሕርይ ወሰዷል፤ ወይም ከአዳም የውርስ ኀጢአትን *(original sin)* ወርሷል ብለን አናምንም።

አንቀጽ 10

የኢየሱስ ክርስቶስን ገቢራዊና ተገብሮአዊ *(active and passive)* መታዘዝን እናምናለን። ይህም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም በሆነው ሕይወቱ የሕግን የጽድቅ መስፈርቶች ለእኛ ሲል በሙላት መፈጸሙንና በመስቀል ላይ ሞቱ የኀጢአታችንን ቅጣት እንደ ተሸከመ እናምናለን።[10]

ኢየሱስ ክርስቶስ በየትኛውም ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕግ መታዘዝ ወይም መፈጸም ሳይችል ቀርቷል ብለን አናምንም። የምግባር ሕግንም ሽሮታል ብለን አናምንም።

---

9 ስለዚህ ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣ ሞትም በኀጢአት በኩል ገብቷል፤ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤ . . . ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን አይደለም፤ በአንድ ሰው መተላለፍ ብዙዎቹ ከሞቱ፣ የእግዚአብሔር ጸጋና በአንዱ ሰው፣ ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የመጣው ስጦታ ለብዙዎች እንዴት አብልጦ ይትረፈረፍ! ደግሞም የእግዚአብሔር ስጦታ እንደ አንዱ ሰው የኀጢአት ውጤት አይደለም፤ ምክንያቱም ፍርዱ የአንድን ሰው ኀጢአት ተከትሎ ኵነኔን አመጣ፤ ስጦታው ግን አያሌ መተላለፍን ተከትሎ ጽድቅን አመጣ። በአንድ ሰው መተላለፍ ምክንያት ሞት በዚህ ሰው በኩል የነገሠ ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ ጸጋና የጽድቅ ስጦታ የተቀበሉት፣ በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት አብልጠው በሕይወት አይነግሡ! ከእንግዲህ በአንድ ሰው መተላለፍ የተነሣ ኵነኔ በሁሉ ሰው ላይ እንደ መጣ፣ እንዲሁም በአንዱ የጽድቅ ሥራ ለሰው ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ጽድቅ ተገኘ። በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ፣ በአንዱ ሰው መታዘዝ ደግሞ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። ሕግ በመምጣቱ መተላለፍ በዛ፤ ነገር ግን ኀጢአት በበዛበት ጸጋ አብልጦ የተትረፈረፈ ሆነ፤ ይህም የሆነው ኀጢአት በሞት እንደ ነገሠ ሁሉ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ደግሞ የዘላለም ሕይወት ይገኝ ዘንድ ጸጋ በጽድቅ እንዲነግሥ ነው (ሮሜ 5፥12–21)። በተጨማሪም፣ 1 ቆሮንቶስ 15፥22፣ 45–49፤ ኤፌሶን 2፥14–16፤ 5፥23፤ ቈላስይስ 1፥18ን ይመልከቱ።

10 በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ፣ በአንዱ ሰው መታዘዝ ደግሞ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ (ሮሜ 5፥19)። በተጨማሪም፣ ማቴዎስ 3፥15፤ ዮሐንስ 8፥29፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥21፤ ፊልጵስዩስ 2፥8፤ ዕብራውያን 5፥8ን ይመልከቱ።

አንቀጽ 11

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕዝቡ ኀጢአት ራሱን በመስቀል ላይ ምትካዊ የስርየት *መሥዋዕት* *(penal substitutionary atonement)* አድርጎ ማቅረቡን እናምናለን። በዚህም የእግዚአብሔርን ቍጣ ማስተሰረዩን፣ የእግዚአብሔርን ፍትሕ ማርካቱን፣ እንዲሁም በኀጢአት፣ በሞትና በሰይጣን ላይ ድል መቀዳጀቱን እናምናለን።[11]

የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ለሰይጣን የተከፈለ ቤዛ ነው ብለን አናምንም። የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ምሳሌ ብቻ፣ ወይም በሰይጣን ላይ የተቀዳጀው ድል ብቻ፣ አልያም የእግዚአብሔር ምግባራዊ አስተዳደር ማሳያ ብቻ ነው ብለን አናምንም።

አንቀጽ 12

የእኛ ኀጢአት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚቈጠርበት፣ የርሱ ጽድቅ ደግሞ በእምነት ለእኛ የሚቈጠርበትን *(double imputation)* አስተምህሮ እናምናለን።[12]

ኀጢአት ያለ ፍርድ ይታለፋል ብለን አናምንም። ገቢራዊው የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ታዛዥነት ለእኛ አይቈጠርም ብለን አናምንም።

አንቀጽ 13

በሦስተኛው ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣና በሥጋ ለብዙዎች እንደ ታየ እናምናለን።[13]

ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተ መሰለ እንጂ አልሞተም፣ ወይም መንፈሱ ብቻ ነው በሕይወት የተነሣው፣ አልያም ትንሣኤው የተከናወነው በተከታዮቹ ልብ ውስጥ ብቻ ነው ብለን አናምንም።

---

11 በደሙም በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማስተሰረያ *መሥዋዕት* አድርጎ አቅርቦታል፤ ይህንም ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን ኀጢአት ሳይቀጣ በትዕግሥት በማለፍ ጽድቁን ለማሳየት ነው፤ በአሁኑ ዘመን እግዚአብሔር ይህን ያደረገው፣ ጽድቁን ይኸውም እርሱ ራሱ ጻድቅ ሆኖ፣ በኢየሱስ የሚያምነውን የሚያጸድቅ መሆኑን ለማሳየት ነው (ሮሜ 3፥25–26)። በተጨማሪም፣ ኢሳይያስ 53፤ ሮሜ 5፥6፣ 8፣ 15፤ 6፥10፤ 7፥4፤ 8፥34፤ 14፥9፣ 15፤ 1 ቆሮንቶስ 15፥3፤ ኤፌሶን 5፥2፤ 1 ተሰሎንቄ 5፥10፤ 2 ጢሞቴዎስ 2፥11፤ ዕብራውያን 2፥14፣ 17፤ 9፥14–15፤ 10፥14፤ 1 ጴጥሮስ 2፥24፤ 3፥18፤ 1 ዮሐንስ 2፥2፤ 3፥8፤ 4፥10ን ይመልከቱ።

12 እኛ በርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው (2 ቆሮንቶስ 5፥21)። በተጨማሪም፣ ማቴዎስ 5፥20፤ ሮሜ 3፥21–22፤ 4፥11፤ 5፥18፤ 1 ቆሮንቶስ 1፥30፤ 2 ቆሮንቶስ 9፥9፤ ኤፌሶን 6፥14፤ ፊልጵስዩስ 1፥11፤ 3፥9፤ ዕብራውያን 12፥23ን ይመልከቱ።

13 እኔ የተቀበልሁትንና ከሁሉ በላይ የሆነውን ለእናንተ አስተላልፌአለሁ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤ ከዚያም ለኬፋ ታየ፤ ቀጥሎም ለዐሥራ ሁለቱ ታየ (1 ቆሮንቶስ 15፥3–5)። በተጨማሪም፣ ኢሳይያስ 53፤ ማቴዎስ 16፥21፤ 26፥32፤ 28፥1–10፤ ዮሐንስ 21፥14፤ ሐዋርያት 1፥9–11፤ 2፥25፣ 32፤ 3፥15፣ 26፤ 4፥10፤ 5፥30፤ 10፥40፤ ሮሜ 4፥24–25፤ 6፥9–10፤ ኤፌሶን 4፥8–10ን ይመልከቱ።

አንቀጽ 14

ኢየሱስ ክርስቶስ በመክበሩ የትንሣኤ በኵር እንደ ሆነ፣ ኀጢአትንና ሞትን ድል እንዳደረገ፣ እንዲሁም ከርሱ ጋራ ባለን አንድነት እኛም እንደምንነሣ እናምናለን።[14]

የኢየሱስ ክርስቶስ የከበረ የትንሣኤ አካል፣ በአትክልት ስፍራው መቃብር ውስጥ ከነበረው አካል ፈጽሞ የተለየ ነው ብለን አናምንም። የእኛ ትንሣኤ ከአካል ውጪ የሚሆን የመንፈሳችን ትንሣኤ ብቻ ነው ብለንም አናምንም።

አንቀጽ 15

ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ወደሚገኘው ሰማያዊ ዙፋኑ ማረጉን፣ አሁን እንደ ንጉሥ እየገዛ መሆኑን፣ ደግሞም በኀይልና በክብር ለሁሉም በሚታይ ሁኔታ እንደሚመለስ እናምናለን።[15]

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መመለሻው ጊዜ ተሳስቷል ብለን አናምንም።

አንቀጽ 16

ኢየሱስ ክርስቶስ በበዓለ ሀምሳ ዕለት መንፈሱን እንዳፈሰሰ እናምናለን። በአሁኑ ጊዜ በዙፋኑ ተቀምጦ ሁሉን እየገዛ፣ ስለ ሕዝቡ እየማለደና እርሱ ብቻ ራስ የሆነላትን ቤተ ክርስቲያኑን እየሠራ እንደ ሆነ እናምናለን።[16]

ኢየሱስ ክርስቶስ የሮምን ጳጳስ እንደ እንደ ራሴው ሾሟል፣ ወይም ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጪ ማንም ሰው የቤተ ክርስቲያን ራስ ሊሆን ይችላል ብለን አናምንም።

---

14 ነገር ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኵራት ሆኖ በርግጥ ከሙታን ተነሥቷል። . . . "ሞት ሆይ፤ ድል መንሣትህ የት አለ? ሞት ሆይ፤ መንደፊያህስ የት አለ?" (1 ቆሮንቶስ 15፥20፣ 55)። በተጨማሪም፣ ሮሜ 5፥10፤ 6፥4፣ 8፣ 11፤ 10፥9፤ 1 ቆሮንቶስ 15፥23፤ 2 ቆሮንቶስ 1፥9፤ 4፥10–11፤ ኤፌሶን 2፥6፤ ቈላስይስ 2፥12፤ 2 ተሰሎንቄ 2፥13፤ ዕብራውያን 2፥9፣ 14፤ 1 ዮሐንስ 3፥14፤ ራእይ 14፥4፤ 20፥14ን ይመልከቱ።

15 እነርሱም ተሰብስበው ሳሉ፣ "ጌታ ሆይ፤ የእስራኤልን መንግሥት መልሰህ የምታቋቁምበት ጊዜው አሁን ነውን?" ብለው ጠየቁት። እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "አብ በገዛ ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜ ወይም ወቅት ማወቁ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።" ይህን ካለ በኋላ እያዩት ወደ ላይ ዐረገ፤ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረችው። እርሱም በሚሄድበት ጊዜ ትኵር ብለው ወደ ሰማይ ሲመለከቱ፣ እነሆ፤ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ድንገት አጠገባቸው ቆሙ፤ እንዲህም አሏቸው፤ "እናንተ የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ እዚህ የቆማችሁት ለምንድን ነው? ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያያችሁት ኢየሱስ፣ ልክ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለሳል" (ሐዋርያት 1፥6–11)። በተጨማሪም፣ ሉቃስ 24፥50–53፤ ሐዋርያት 1፥22፤ 2፥33–35፤ ኤፌሶን 4፥8–10፤ 1 ጢሞቴዎስ 3፥16ን ይመልከቱ።

16 እግዚአብሔርም ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛለት፤ በቤተ ክርስቲያንም በማንኛውም ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾመው (ኤፌሶን 1፥22)። በተጨማሪም፣ ሐዋርያት 2፥33፤ 1 ቆሮንቶስ 11፥3–5፤ ኤፌሶን 4፥15፤ 5፥23፤ ቈላስይስ 1፥18ን ይመልከቱ።

አንቀጽ 17

ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎች ሁሉ ላይ ለመፍረድ በክብር እንደሚመጣ፣ ጠላቶቹን ሁሉ በመጨረሻ እንደሚያሸንፍ፣ ሞትን እንደሚያጠፋ፣ እንዲሁም በጽድቅ የሚነግሥበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን ያበስራል ብለን እናምናለን።

የኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻ መመለስ በ70 ዓ.ም. (AD 70) ተፈጽሟል፤ ወይም መምጣቱና ተያያዥ ክሥተቶች ምሳሌያዊ ብቻ ናቸው ብለን አናምንም።[17]

አንቀጽ 18

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚያምኑ ወደ ዘላለማዊ መንግሥቱ እንደሚገቡ፣ ነገር ግን በርሱ የማያምኑ በገሃነም ውስጥ ዘላለማዊ የሆነ ቅጣት *(conscious punishment)* እንደሚቀበሉ እናምናለን።

ሁሉም ሰው ይድናል ብለን አናምንም። በኢየሱስ ክርስቶስ ሳያምኑ የሚሞቱ ሰዎች ከህልውና ውጪ ሆነው ይጠፋሉ *(annihilated)* ብለን አናምንም።

አንቀጽ 19

ዓለም ሳይፈጠር በኢየሱስ ክርስቶስ የተመረጡና በእምነት ከርሱ ጋራ አንድ የሆኑ ሁሉ፣ ከርሱ ጋራና እርስ በርሳቸው ኅብረት እንዳላቸው እናምናለን። መጽደቅን፣ ልጅነትን፣ መቀደስንና መክበርን ጨምሮ[18] መንፈሳዊ በረከትን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደምናገኝ እናምናለን።[19]

ኢየሱስ ክርስቶስና የማዳን ሥራው ሊነጣጠሉ ይችላሉ ብለን አናምንም። ከራሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጪ በሆነ መንገድ የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ሥራ ተካፋይ መሆን እንችላለን ብለን አናምንም። ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ አንድ ሆነን ከርሱ አካል፣ ማለትም ከቤተ ክርስቲያን ጋራ አንድ ላንሆን እንችላለን ብለን አናምንም።

---

17 ለሕዝቡ እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታንም ላይ እንዲፈርድ እግዚአብሔር የሾመው እርሱ መሆኑን እንድንመሰክር እርሱ ራሱ አዘዘን (ሐዋርያት ሥራ 10፥42)። በተጨማሪም፣ ዮሐንስ 12፥48፤ 14፥3፤ ሐዋርያት 7፥7፤ 17፥31፤ 2 ጢሞቴዎስ 4፥1፣ 8ን ይመልከቱ።

18 የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፤ እነርሱም ለኀጢአት ምክንያት የሆኑትንና ክፉ የሚያደርጉትን ሁሉ ለቅመው ከመንግሥቱ ያወጣሉ። ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ወደ እቶን እሳት ይጥሏቸዋል። በዚያ ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሓይ ያበራሉ። ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ (ማቴዎስ 13፥41–43)። በተጨማሪም፣ ኢሳይያስ 25፥6–9፤ 65፥17–25፤ 66፥21–23፤ ዳንኤል 7፥13–14፤ ማቴዎስ 5፥29–30፤ 10፥28፤ 18፥8–9፤ ማርቆስ 9፥42–49፤ ሉቃስ 1፥33፤ 12፥5፤ ዮሐንስ 18፥36፤ ቈላስይስ 1፥13–14፤ 2 ተሰሎንቄ 1፥5–10፤ 2 ጢሞቴዎስ 4፥1፣ 18፤ ዕብራውያን 12፥28፤ 2 ጴጥሮስ 1፥11፤ 2፥4፤ ራእይ 20፥15ን ይመልከቱ።

19 አይሁድ ወይም የግሪክ ሰዎች ብንሆን፣ ባሪያ ወይም ነጻ ሰዎች ብንሆን፣ እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና፤ ሁላችንም አንዱን መንፈስ እንድንጠጣ ተሰጥቶናል (1 ቆሮንቶስ 12፥13)። በተጨማሪም፣ ዮሐንስ 14፥20፤ 15፥4–6፤ ሮሜ 6፥1–11፤ 8፥1–2፤ 12፥3–5፤ 1 ቆሮንቶስ 1፥30–31፤ 6፥15–20፤ 10፥16–17፤ 12፥27፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥17–21፤ ገላትያ 3፥25–29፤ ኤፌሶን 1፥3–10፣ 22–23፤ 2፥1–6፤ 3፥6፤ 4፥15–16፤ 5፥23፣ 30፤ ቈላስይስ 1፥18፤ 2፥18–19ን ይመልከቱ።

**አንቀጽ 20**

እግዚአብሔር በራሳችን መልካምነት ወይም ሥራ ሳይሆን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ ላይ ባለን እምነት ብቻ፣ በጸጋው ብቻ ጻድቃን እንደ ሆንን የሚያውጅበትን "በእምነት ብቻ የመጽደቅን" አስተምህሮ እናምናለን። በእምነት ብቻ የመጽደቅን አስተምህሮ መካድ፣ ወንጌልን መካድ መሆኑን እናምናለን።[20]

የምንጸድቀው በውስጣችን በሚጨመር *(infused)* ማንኛውም ጸጋ ነው ብለን አናምንም። የምንጸድቀው በማንነታችን ጻድቅ ሆነን ከተለወጥን በኋላ ብቻ ነው ብለን አናምንም። ይህ መጽደቅ አሁንም ሆነ ወደፊት በእኛ ታማኝነት ላይ የተመሠረተ ነው ብለን አናምንም።

**አንቀጽ 21**

እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ኀይል፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ላይ ተመሥርቶ እኛን ከኀጢአት አገዛዝ ነጻ የሚያወጣበትን፣ የሚለይበትንና ወደ ልጁ መልክ ይበልጥ እየለወጠ ቅዱስ የሚያደርግበትን የመቀደስን *(sanctification)* አስተምህሮ እናምናለን። መቀደስ የእግዚአብሔር የጸጋ ሥራና ከመጽደቅ ጋራ የማይነጣጠል ቢሆንም፣ ከመጽደቅ የተለየ መሆኑን እናምናለን። በዚህ መለኮታዊ የመቀደስ ሥራ ውስጥ እኛ ንቁ ተሳታፊዎች መሆናችንን፣ ለኀጢአት ለመሞትና ለጌታ ለመታዘዝ በምናደርገው ቀጣይነት ያለው ጥረት፣ እግዚአብሔር ላዘጋጃቸው ጸጋ የመቀበያ መንገዶች ራሳችንን የማቅረብ ኀላፊነት እንዳለብን እናምናለን።[21]

አንድ ሰው በመቀደስ ውስጥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ ባለው ኅብረት ወዲያውኑ ፍሬ ሳያፈራ ይጸድቃል ብለን አናምንም። መልካም ሥራዎቻችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር የሚቀበላቸው ቢሆንም፣ ለመጽደቅ ብቃት ይሆኑናል ብለን አናምንም። ምንም እንኳ ከኀጢአት አገዛዝ ነጻ የወጣን ቢሆንም፣ በዚህ ሕይወት ውስጥ ከውስጣዊ ኀጢአት ጋራ የምናደርገው ትግል ያቆማል ብለን አናምንም።

---

20 እንግዲህ በእምነት ስለ ጸደቅን፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋራ ሰላም አለን (ሮሜ 5፥1)። በተጨማሪም፣ ሉቃስ 18፥14፤ ሮሜ 3፥24፤ 4፥5፤ 5፥10፤ 8፥30፤ 10፥4፣ 10፤ 1 ቆሮንቶስ 6፥11፤ 2 ቆሮንቶስ 5፥19፣ 21፤ ገላትያ 2፥16–17፤ 3፥11፣ 24፤ 5፥4፤ ኤፌሶን 1፥7፤ ቲቶ 3፥5፣ 7ን ይመልከቱ።

21 በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ 4በፊቱ ቅዱስና እንከን አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በርሱ መርጦናልና (ኤፌሶን 1፥3–4)። በተጨማሪም፣ ዮሐንስ 17፥17፤ ሐዋርያት 20፥32፤ ሮሜ 6፥5–6፣ 14፤ 8፥13፤ 1 ቆሮንቶስ 6፥11፤ 2 ቆሮንቶስ 7፥1፤ ገላትያ 5፥24፤ ኤፌሶን 3፥16–19፤ 4፥23–24፤ ፊልጵስዩስ 3፥10፤ ቈላስይስ 1፥10–11፤ 2 ተሰሎንቄ 2፥13፤ ዕብራውያን 12፥14ን ይመልከቱ።

አንቀጽ 22

ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ብቸኛው መካከለኛ መሆኑን እናምናለን። ዝቅ በማለቱም ሆነ በመክበሩ ሁኔታ የኢየሱስ ክርስቶስን የነቢይነት፣ የካህንነትና የንጉሥነት አገልግሎት እናምናለን። በአባቱ የተጠራበትን ይህን የመካከለኛነት አገልግሎት ለመፈጸም በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተቀባም እናምናለን።[22]

እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸው ሌሎች የሥጋ መገለጦች *(incarnations)* ነበሩት ወይም ይኖሩታል ብለን አናምንም፤ ወይም ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ውጪ ሌሎች የመቤዠት መካከለኞች አሉ ወይም ይኖራሉ ብለን አናምንም። ከኢየሱስ ክርስቶስ ውጪ ድነት አለ ብለን አናምንም።

አንቀጽ 23

እንደ ታላቁ የእግዚአብሔር ነቢይ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የትንቢት ርእስ ጉዳይም ፍጻሜም መሆኑን እናምናለን። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደ ገለጠና እንደ ዐወጀ፣ የወደ ፊት ክሥተቶችን እንደ ተነበየ፣ ደግሞም እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ተስፋዎች ፍጻሜ መሆኑን እናምናለን።[23]

ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሰተኛ ትንቢት ወይም ሐሰተኛ ቃል ተናግሯል፣ ወይም ስለ ራሱ የተነገሩ ትንቢቶችን መፈጸም ተስኖታል ወይም ይሳነዋል ብለን አናምንም።

---

22 አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ መካከለኛ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው (1 ጢሞቴዎስ 2፥5)። በተጨማሪም፣ ኢዮብ 33፥23-28፤ ሉቃስ 1፥33፤ ዮሐንስ 1፥1-14፤ 14፥6፤ ሐዋርያት 3፥22፤ ቈላስይስ 1፥15፤ ዕብራውያን 1፥1-4፤ 5፥5-6፤ 9፥15፤ 12፥24ን ይመልከቱ።

23 አሁንም ወንድሞች ሆይ፤ እናንተ ይህን ያደረጋችሁት እንደ አለቆቻችሁ ሁሉ ባለማወቅ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ። እግዚአብሔር ግን የርሱ የሆነው ክርስቶስ መከራን እንዲቀበል አስቀድሞ በነቢያቱ ሁሉ አፍ የተናገረውን ፈጽሟል። እንግዲህ ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሓ ግቡ፤ ከመንገዳችሁም ተመለሱ፤ ከጌታም ዘንድ የመታደስ ዘመን ይመጣላችኋል፤ ደግሞም አስቀድሞ ለእናንተ የተመደበውን ክርስቶስን፣ እርሱም ኢየሱስን ይልክላችኋል። እግዚአብሔር አስቀድሞ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ እንደ ተናገረ፣ ሁሉን ነገር እስከሚያድስበት ዘመን ድረስ እርሱ በሰማይ ይቈይ ዘንድ ይገባል። ሙሴም እንዲህ ብሏል፤ ‘ጌታ አምላካችሁ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ከወንድሞቻችሁ መካከል ያስነሣላችኋል፤ እርሱ የሚነግራችሁን ሁሉ ስሙት (ሐዋርያት 3፥17-22)። በተጨማሪም፣ ማቴዎስ 20፥17፤ 24፥3፤ 26፥31፣ 34፣ 64፤ ማርቆስ 1፥14-15፤ ሉቃስ 4፥18-19፣ 21፤ ዮሐንስ 13፥36፤ 21፥22፤ 1 ቆሮንቶስ 1፥20፤ ዕብራውያን 1፥2፤ ራእይ 19፥10ን ይመልከቱ።

አንቀጽ 24

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዐት ታላቁ ሊቀ ካህናችን መሆኑን፣ ራሱን ፍጹም መሥዋዕት አድርጎ ስለ እኛ ማቅረቡን፣ ደግሞም በአብ ፊት ስለ እኛ መማለዱን እንደ ቀጠለ እናምናለን። ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቁ የኀጢአት ማስተስረያ መሥዋዕት አቅራቢም መሥዋዕትም መሆኑን እናምናለን።[24]

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ከይሁዳ ነገድ እንጂ ከሌዊ ነገድ ስላልሆነ፣ ካህናችን ሆኖ ለማገልገል ብቁ አይደለም ብለን አናምንም። በቅዳሴ ሥርዐት ውስጥ ደም በማይፈስበት መንገድ እንኳ ቢሆን፣ እንደ መሥዋዕትና እንደ ካህን ራሱን ደጋግሞ መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል ብለን አናምንም። እርሱ ካህን የሆነው በሰማይ ብቻ ነው እንጂ በምድር ላይ ካህን አልነበረም ብለን አናምንም።

አንቀጽ 25

እንደ ንጉሥ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድራዊና በሰማያዊ ኀይላት ሁሉ ላይ አሁንና ለዘላለም በሉዓላዊነት እንደሚነግሥ እናምናለን።[25]

የኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት የዚህ ዓለም ፖለቲካዊ መንግሥት ብቻ ናት ብለን አናምንም። ምድራዊ ገዥዎች ለርሱ ተጠያቂ አይደሉም ብለን አናምንም።

---

24 ክርስቶስ የእውነተኛዪቱ ድንኳን ምሳሌ ወደ ሆነችውና በሰው እጅ ወደ ተሠራችው መቅደስ አልገባም፤ ነገር ግን አሁን ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት ወደ እርሷ፣ ወደ ሰማይ ገባ። ሊቀ ካህናት የራሱ ያልሆነውን ደም ይዞ በየዓመቱ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንደሚገባ፣ ክርስቶስ ራሱን ብዙ ጊዜ መሥዋዕት ለማድረግ ወደ ሰማይ አልገባም። እንዲህ ቢሆን ኖሮ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ መከራን መቀበል ባስፈለገው ነበር። አሁን ግን በዘመናት መጨረሻ ራሱን መሥዋዕት በማድረግ ኀጢአትን ለማስወገድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተገልጧል። ሰው አንድ ጊዜ ሊሞት ከዚያም በኋላ በፍርድ ፊት ሊቆም ተወስኖበታል። ክርስቶስ የብዙ ሰዎችን ኀጢአት ለመሸከም፣ እንዲሁ አንድ ጊዜ መሥዋዕት ሆኗል፤ ሁለተኛ ጊዜም ይገለጣል፤ ይህም ለሚጠባበቁት ድነትን ለማምጣት እንጂ ኀጢአትን ለመሸከም አይደለም (ዕብራውያን 9፥24–28)። በተጨማሪ፣ ዮሐንስ 1፥36፤ 19፥28–30፤ ሐዋርያት 8፥32፤ 1 ቆሮንቶስ 5፥7፤ ዕብራውያን 2፥17–18፤ 4፥14–16፤ 7፥25፤ 10፥12፣ 26፤ 1 ጴጥሮስ 1፥19፤ ራእይ 5፥6፣ 8፣ 12–13፤ 6፥1፣ 16፤ 7፥9–10፣ 14፣ 17፤ 8፥1፤ 12፥11፤ 13፥8፤ 15፥3ን ይመልከቱ።

25 ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስከሚያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና (1 ቆሮንቶስ 15፥25)። በተጨማሪም፣ መዝሙር 110፤ ማቴዎስ 28፥18–20፤ ሉቃስ 1፥32፤ 2፥11፤ ሐዋርያት 2፥25፣ 29፣ 34፤ 4፥25፤ 13፥22፣ 34፣ 36፤ 15፥16፤ ሮሜ 1፥3፤ 2 ጢሞቴዎስ 2፥8፤ ዕብራውያን 4፥7፤ ራእይ 3፥7፤ 5፥5፤ 22፥16ን ይመልከቱ።

አንቀጽ 26

ኢየሱስ ክርስቶስ ጠላቶቹን ሁሉ ድል ሲያደርግ፣ መንግሥቱን ለአብ እንደሚያስረክብ እናምናለን። በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋራ እንደሚሆን፣ አማኞችም ኢየሱስ ክርስቶስን ፊት ለፊት እንደሚያዩት፣ እርሱን እንደሚመስሉና በርሱም ለዘላለም ደስ እንደሚሰኙ እናምናለን።[26]

ለሰው ልጅ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ ተስፋ፣ ወይም ድነት የሚገኝበት ሌላ ስም ወይም መንገድ አለ ብለን አናምንም።

---

26 ከዚያም ግዛትን፣ ሥልጣንና ኀይልን ሁሉ ከደመሰሰ በኋላ መንግሥትን ለእግዚአብሔር አብ ሲያስረክብ፣ ያን ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል፤ ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስከሚያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና፤ የሚደመሰሰውም የመጨረሻው ጠላት ሞት ነው። “ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛህለት”፤ ነገር ግን፣ “ሁሉን አስገዛለት” ሲል፣ ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆኑ ግልጽ ነው። 28ሁሉ ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ እንዲሆን ወልድ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ለርሱ ይገዛል (1 ቆሮንቶስ 15፥24-28)። በተጨማሪም፣ ኢሳይያስ 65፥17፤ 66፥22፤ ፊልጵስዩስ 2፥9-11፤ 2 ጴጥሮስ 3፥13፤ 1 ዮሐንስ 3፥2-3፤ ራእይ 21፥1-5፤ 22፥1-5ን ይመልከቱ።

# የማብራሪያ ጽሑፍ

ከአጠቃቀም
መመሪያዎች ጋራ

አንድ ቀን መላው ምድር፣ “ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው” በሚል አንድ ብቸኛ የእምነት ቃል ያስተጋባል (ፊልጵስዩስ 2፥11)። ይህች ዐጭር ዐረፍተ ነገር ትርጕሟ ጥልቅ ነው። ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ማለት፣ እርሱ “የተቀባው” ነው ማለት ነው። እርሱ ተስፋ የተገባውና ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው መሲሕ ነው ማለት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው ማለት፣ እርሱ እውነተኛ አምላክ መሆኑን መናገር ነው። ተሠግዎ የድንቆች ድንቅና አስደናቂ ምስጢር ነው። እግዚአብሔር ሥጋ ሆነ። እርሱን ኢየሱስ ብሎ መጥራት እንኳ፣ እርሱ ብቸኛው አዳኝ መሆኑን መናገር ነው። ሕዝቡን ከኀጢአታቸው የማዳን ተልእኮን ለመፈጸም ወደ ዓለም መጣ (ማቴዎስ 1፥21)።

“ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው” የሚለው ዐረፍተ ነገር፣ ዐጭር የእምነት መግለጫ (*Creed*) ነው። የእንግሊዘኛው Creed የሚለው ቃል የመጣው “አምናለሁ” የሚል ትርጕም ካለው ክሬዶ (*Credo*) ከሚለው የላቲን ቃል ነው። ይህ ዐጭር መግለጫ ስለ ክርስቶስ የምናምነውን ያውጃል። አንዳንዶች 1 ጢሞቴዎስ 3፥16 በተመሳሳይ የእምነት መግለጫ ሊሆን እንደሚችል ያስባሉ። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ይቀርባሉ። የመጀመሪያው፣ ጳውሎስ፣ “የእግዚአብሔር አምልኮ ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው” የሚለውን አገላለጽ ይጠቀማል። ሁለተኛው፣ የዚህ ጥቅስ ሐረጎች ዜማ ያላቸውና በግጥም መልክ የተቀመጡ ናቸው። እነዚህ ሐረጎች በሥጋ የተገለጠውን ክርስቶስን በዐጭሩ ጠቅለል ባለ መልኩ ይገልጡታል፡-

> እርሱ በሥጋ ተገለጠ፤
> በመንፈስ ጸደቀ፤
> በመላእክት ታየ፤
> በአሕዛብ ዘንድ ተሰበከ፤
> በዓለም ባሉት ታመነ፤
> በክብር ዐረገ። (1 ጢሞቴዎስ 3፥16)

መጽሐፍ ቅዱሳዊው ንድፉ አስፈላጊ ነው። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎችንና የእምነት መግለጫዎችን ባዘጋጀች ጊዜ፣ እምነትን ለመመስከር አዲስ ዘዴ መፍጠሯ አልነበረም። ይልቁንም፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለውን ትውፊት እያስቀጠለች ነበር።

ተግዳሮቶች ሲነሡ፣ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አቋም ትወስድ ነበር። በተጨማሪም፣ ብዙዎች እንደሚያስቡት የሥርዐተ አምልኮ አስፈልጎቶች ወይም ንጹሕ አምልኮን የመፈለግ ጽኑ መሻት፣ ቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎችን እንድትጽፍ ገፋፍተዋታል። ይህ በተለይም አስተምህሮ ክርስቶስን በሚመለከት እውነት ነው። የኢየሱስ ማንነትና ሥራ መሠረታዊ እውነት፣ ባለፉት ክፍለ ዘመናት ሁሉ የክርስትና መለያ ምልክት ሆኖ ቈይቷል።

የአዲስ ኪዳን ጸሓፊዎች ራሳቸው የክርስቶስን ማንነትና ሥራን በተመለከተ ከተነሡ የሐሰት ሐሳቦች ጋራ ተጋድለዋል። በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ክፍለ ዘመናት፣ የተለያዩ ቡድኖች የክርስቶስን እውነተኛ ሰብአዊነት ተቃውመው ነበር። ዶሴቲስቶች ኢየሱስ ሰው "ይመስላል" እንጂ ሰው አልነበረም በማለት ተናግረዋል። እንደ አርዮሳውያን ያሉ ሌሎች መናፍቃን ደግሞ የክርስቶስን እውነተኛ አምላክነት ተቃወመዋል። እነዚህ መናፍቃን እርሱ ከእግዚአብሔር አብ ያነሰ መሆኑን ተናግረዋል። በኋላ የተነሡ ቡድኖች ደግሞ፣ ሁለቱ ባሕርያት፣ ማለትም እውነተኛ ሰውነትና እውነተኛ አምላክነት በአንዱ አካል /ማንነት/ ውስጥ እንዴት በአንድነት እንዳሉ በመግለጽ ረገድ ስሕተት ሠርተዋል። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ለእነዚህ ተግዳሮቶችና ስሕተቶች ምላሽ የሰጠችው፣ ጉባኤዎችን በመጥራትና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቲያናዊ እምነት ማዕከላዊ እውነቶች የሚያስተምረውን የሚጠቀልሉ የእምነት መግለጫዎችን በመጻፍ ነበር። እነዚህ የእምነት መግለጫዎች ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው የተላለፉ ትልቅ ቅርስ ናቸው። ስለዚህ ዛሬ፣ የሐዋርያት የእምነት መግለጫ፣ የኒቂያ የእምነት መግለጫና የኬልቄዶን መግለጫ ግብአቶች አሉን። እነዚህ የእምነት መግለጫዎች፣ በርቱዕነትና በመናፍቅነት መካከል ግልጽ መስመር የሚሥሉ የድንበር ምልክቶች ናቸው።

እነዚህ መግለጫዎች ቤተ ክርስቲያንን ለማጠናከር ያገለገሉ ሲሆን፣ በጸጋውና በሉዓላዊው የእግዚአብሔር እጅ፣ ክርስቲያኖች ወንጌልን በታማኝነት እንዲያውጁ መርተዋል። ዛሬም ለዘላቂ ዋጋቸው ምስክርነት ይነበባሉ። ክርስቶስ በነገረ መለኮታችንና በአምልኳችን ማዕከል ላይ መሆኑንም ያስታውሱናል። እነዚህ መግለጫዎች ቤተ ክርስቲያንን "ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ ተሰጠው እምነት እንድትጋደል" ይጠሩአታል (ይሁዳ 1፥3)።

ሆኖም፣ እነዚህ የእምነት መግለጫዎች የክርስቶስን ሥራ የሚጠቊሙት በጥቂቱ ነው። ወንጌልን ሙሉ በሙሉ አያብራሩም። በሚታየው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛ ክፍፍል የተፈጠረው በተሐድሶው *(Reformation)* ዘመን ነበር። ቊልፍ ጉዳዩ የክርስቶስ ሥራ ነበር። በተለይም፣ በእምነት ብቻ መጽደቅ

በሚለው አስተምህሮ ዙሪያ የተነሣው ክርክር የተሐድሶውን እንቅስቃሴ የጫረው ማዕከላዊ ውዝግብ ነበር። በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በፕሮቴስታንት እና በሮማ ካቶሊክ በሁለት ጐራ ተከፈለች። ፕሮቴስታንትነት "በእምነት ብቻ መጽደቅን" ሲያረጋግጥ፣ የሮማ ካቶሊክ ግን፣ የትሬንት ጉባኤ ድንጋጌዎችን ተከትሎ፣ በእምነት ብቻ መጽደቅን ተቃውሟል። ደግሞም፣ መጽደቅን የእምነትና የሥራ ትብብር ውጤት አድርጎ መመልከትን መረጠ። ተሐድሶው በሌላ ጉዳይም ላይ ልዩነትን አሳይቷል። ይኸውም፣ በቤተ ክርስቲያኑ ላይና በነገር ሁሉ ላይ ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ የበላይ እና ብቸኛ ራስነት ጉዳይ ነው።

በአጠቃላይ፣ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዓለም ዐቀፋዊ የእምነት መግለጫዎችና እነዚህ የተሐድሶው ትኩረቶች፣ ቤተ ክርስቲያን ለመጽሐፍ ቅዱስ ታማኝ የሆነ ወንጌልን እንድታውጅ መመሪያዎችን ይሰጣሉ። የእምነት መግለጫዎች፣ የተለያዩ የተሐድሶው የተብራሩ የእምነት መግለጫዎች *(Confessions)* እና የእምነት ማስተማሪያዎች *(Catechisms)* የእምነት ማጠቃለያዎችን ያቀርባሉ፤ ለእምነትና ለወንጌልም ግልጽነትን ያመጣሉ።

"ቃል ሥጋ ሆነ፦ የሊጎኔር የነገረ ክርስቶስ የእምነት መግለጫ" ያለፉትን ዘመናት ሀብቶች፣ ማለትም ሁለቱንም የጥንት የእምነት መግለጫዎችንና የተሐድሶ ነገረ መለኮትን በመጠቀም፣ ለዚህ ትውልድ ቤተ ክርስቲያንና እግዚአብሔር ቢፈቅድ ለሚመጡት ትውልዶች፣ የክርስቶስ ማንነትና ሥራን በተመለከተ ዐጠር ያለ መግለጫ በትሕትና ለማቅረብ ይሞክራል። ምናልባት ይህ መግለጫና ዐብረውት ያሉት ሃያ ስድስቱ የምናምናቸውንና የማናምናቸውን ነገሮች የሚገልጹ አንቀጾች፣ በእነዚህ ወሳኝ የነገረ ክርስቶስ ጉዳዮች ላይ ለበለጠ ውይይትና ምልከታዎች እንደ መነሻ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ምናልባትም ይህ መግለጫ ራሱ፣ ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ይህ መግለጫ በጋራ ለሚደረግ ሕዝባዊ ንባብ ተስማሚ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ይህን መግለጫ የሚያገኝ ማንኛውም ሰው "ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው" የሚለውን እውነት እንዲያውቅ እንፈልጋለን።

## ስለ መግለጫው

መግለጫው ስድስት አንጓዎች ወይም ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው እንደ መቅድም ያገለግላል፤ በውስጡም ሁለት ቊልፍ ግሦች አሉ፤ እነርሱም፣ "እንመሰክራለን" እና "ደስ ይለናል" ናቸው። እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን በቅዱሳት መጻሕፍት ገጾች ውስጥ ገልጧል። ሆኖም፣ አሁንም ለርሱ ብቻ የሆኑ "ምስጢራት" (ዘዳግም 29፥29) አሉ። በነገረ መለኮት ተግባር ውስጥ ሁልጊዜ ውስንነቶቻችንን ማሰብ አለብን። ስለዚህ የወንጌሉን ምስጢርና ድንቅ በመመስከር እንጀምራለን። የዚህ መግለጫ ዋና ትኩረት

ተሠግዎ ነው፤ ይህንም እግዚአብሔር ሥጋ ሆነ በሚሉት ቃላት ዐጠር አድርገን እንገልጸዋለን። የክርስቶስ ማንነት ወዲያውኑ ወደ ክርስቶስ ሥራ ይመራናል፣ ስለዚህ በክርስቶስ የማዳን ሥራ ሁላችንም በጋራ ደስ ይለናል።

ሁለተኛው አንቀጽ የክርስቶስን እውነተኛ አምላክነት ያጐላል፤ በሦስቱ የሥላሴ አካላት መካከል እኩል ቦታ እንዳለው ይመለከታል። ይህ አንቀጽ ከኬልቄዶን ውሳኔ የተወሰደውን የኬልቄዶን ቀመር (Formula) እንደ ገና በመግለጽ ይጠናቀቃል። ክርስቶስ ሰው ከሆነ ጊዜ ጀምሮ እርሱ ለዘላለም ሁለት ባሕርያት ያሉት አንድ አካል ነው።

የተሠግዎ ማብራሪያ ሦስተኛውን አንቀጽ ይይዛል፤ ይህም የክርስቶስን እውነተኛ ሰውነት ያጐላል። እርሱ ተወለደ። እርሱ አማኑኤል ነው፣ ትርጕሙም፣ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ" ማለት ነው (ማቴዎስ 1፥23)። እዚህ ላይ የርሱን ሞት፣ መቀበር፣ ትንሣኤ፣ ዕርገትና ዳግም መምጣት እንመሰክራለን። እነዚህ የተሠግዎ ታሪካዊ እውነታዎች ናቸው።

የተሠግዎ ነገረ መለኮታዊ እውነታዎች በአራተኛው ክፍል ይከተላሉ፤ ይህም ከተሐድሶው ዘመን በተገኙ መረዳቶች ላይ ይደገፋል። በእኛ ፈንታ፣ ኢየሱስ ፍጹም ታዛዥ ነበር። እርሱ ሕጉን ጠበቀ (ገቢራዊ ታዛዥነት/*active obedience*)፤ ደግሞም፣ የሕጉን ቅጣት ከፈለ (ተገብሮአዊ ታዛዥነት/*passive obedience*)። እርሱ ነውር የሌለበት በግ ነበር፤ ስለ እኛ ምትካዊ የስርየት ቅጣትን ተቀበለ። መላው የሰው ልጅ የተጋፈጠውን እጅግ አስጨናቂ ችግር ፈታ። ይህም የቅዱሱ እግዚአብሔር ቍጣ ነው። ይህ አንቀጽ ጻድቅ ተደርጎ የመቈጠርን አስተምህሮ በማወጅ ይጠናቀቃል። ኀጢአታችን በክርስቶስ ላይ ተቈጠረ፣ የርሱ ጽድቅ ደግሞ ለእኛ ተቈጠረ። እኛ ከእግዚአብሔር ጋራ ሰላም ያለን በክርስቶስ ሥራ ምክንያት ብቻና ብቻ ነው። የርሱን ጽድቅ እንድንለብስ ተደርጓል።

የክርስቶስ ሦስቱ ሹመቶች (*munus triplex*) የክርስቶስን ሥራ በዐጭሩ የሚገልጽ ጠቃሚ ነገረ መለኮታዊ መዋቅር ነው። በብሉይ ኪዳን የነቢይ፣ የካህንና የንጉሥ ሦስቱ ሹመቶች የተለያዩ የመካከለኛነት ሚናዎች ነበሩ። ኢየሱስ ሦስቱን በአንድ አካሉ ውስጥ አጣምሮ ይዟል፤ ሁሉንም በሙላት ይፈጽማቸዋል። እዚህ ላይ ቀድሞ በመስቀል ላይ የሠራውን የክርስቶስን የመካከለኛነት ሥራ ብቻ ሳይሆን፣ አሁን በአብ ቀኝ እንደ አማላጃችን የሚሠራውን ሥራ እናንጸባርቃለን።

የመደምደሚያው አንቀጽ “ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው” የሚለውን ነጠላውንና ዐጭሩን የእምነት መግለጫ ያረጋግጣል። እውነተኛ ነገረ መለኮት ሁሉ ወደ ምስጋና ወይም አምልኮ ይመራል። ስለዚህ፣ መግለጫው እንባርካለን በሚለው ቊልፍ ግሥ ይጠናቀቃል። አሁን ክርስቶስን በማምለክ፣ ለዘላለማዊ ሥራችን እየተዘጋጀን ነው።

## ሃያ ስድስቱ የምናምናቸውንና የማናምናቸውን ነገሮች የሚገልጹ አንቀጾች

የዚህ መግለጫ ሐረጎች የነገረ ክርስቶስ ጥናት መግቢያዎች ናቸው፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ ያላቸውን ብልጥግና እንድንመረምር ይጋብዙናል። እኛን የበለጠ ለመምራት፣ ሃያ ስድስት የምናምናቸውንና የማናምናቸውን ነገሮች የሚገልጹ አንቀጾች ተጨምረዋል። እያንዳንዱም ከቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ጋራ ቀርቧል። ለእያንዳንዱ አንድ ዋና ጥቅስ ሙሉ ለሙሉ ተጽፏል፤ ሌሎች ደጋፊ ጥቅሶችም ቀርበዋል። እነዚህ አንቀጾች ወሳኝ ናቸው። ስለ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ወሰኖችን ያስቀምጣሉ።

አንቀጽ 1 ተሠግዎን በማረጋገጥ እንደ መቅድም ሆኖ ያገለግላል።

አንቀጽ 2 የክርስቶስን እውነተኛ አምላክነት ያረጋግጣል። ከ3–5 ያሉት አንቀጾች ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን የሁለት ባሕርያት አንድ አካል ነገረ ክርስቶስን ያስቀምጣሉ። ከ6–9 ያሉት አንቀጾች የክርስቶስን እውነተኛ ሰውነት ያብራራሉ። ከ10–26 ያሉት ደግሞ፣ ከክርስቶስ ማንነት ወደ ክርስቶስ ሥራ ይሸጋገራሉ። እነዚህ የሚጀምሩት የድነት አስተምህሮዎችን በማረጋገጥ ሲሆን በሦስቱ የክርስቶስ ሹመቶች ማብራሪያ ይጠናቀቃሉ።

የማናምናቸውን ነገሮች የሚገልጹት ዐረፍተ ነገሮች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። በዚህ በመቻቻል ዘመን አንድን እምነት ለመካድ መድፈር የተለመደ አይደለም፣ ነገር ግን እነዚህ የምናምናቸውንና የማናምናቸውን ነገሮች የሚገልጹ አንቀጾች፣ የትዕቢት መግለጫዎች አይደሉም። ይልቁንም፣ ቤተ ክርስቲያን ደኅንነቱ በተጠበቀውና ጤናማ በሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትምህርት ዐጥር ውስጥ እንድትቈይ ለመርዳት ተስፋ በማድረግ የቀረቡ ናቸው። 2 ዮሐንስ 9፣ “በክርስቶስ ትምህርት የማይኖርና ከትምህርቱ የሚወጣ ሁሉ አምላክ የለውም” ይላል። ይህ የሚያመለክተው ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው የክርስቶስ ትምህርት መውጣትን፣ ወይም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከተገለጠው የነገረ ክርስቶስ ወሰን ማለፍን ነው። ሃያ ስድስቱ አንቀጾች የመግለጫውን

የተለያዩ መስመሮች ሲያብራሩ፣ አንቀጾቹ ራሳቸው ወደ ጥልቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስቶስ ትምህርት ሊመሩ ይችላሉ።

አንዳንዶች ለምን አዲስ መግለጫ አስፈለገ ብለው በትክክል ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህ ጥሩ ጥያቄ ነው። ለዚህም መግለጫ ሦስት ምክንያቶችን እናቀርባለን። ጥንታዊና ወቅታዊ ተግዳሮቶችን በመመለስ የቤተ ክርስቲያንን አምልኮና ትምህርት እንደሚያገለግል እንተማመናለን። እንዲሁም በወንጌል አገልግሎት ውስጥ ላሉት በእውነት በአገልግሎት አጋር የሆኑትን ሌሎችን የሚለዩበትን መንገድ ይሰጣል ብለን እናምናለን። በመጨረሻም፣ ለቤተ ክርስቲያን አስቸጋሪ ጊዜያት እየመጡ እንዳሉ ይሰማናል፤ እናም ይህ መግለጫ ሁላችንንም የወንጌልን ዋና ነገር፣ ውበቱን፣ አስፈላጊነቱንና አጣዳፊነቱን፣ እንደሚያስታውሰን እንተማመናለን። እያንዳንዱን ምክንያት ተመልከቱ፡-

## ለአምልኮና ለመታነጽ

ሊጎኔር ይህን መግለጫ ለቤተ ክርስቲያን በትሕትና ያቀርባል። ከመጀመሪያዎቹ ክፍለ ዘመናት ጀምሮ፣ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ አምልኮ ውስጥ የእምነት መግለጫዎችን ተጠቅመዋል። ይህ መግለጫ ለተመሳሳይ ዐላማ ያገለግላል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። የእምነት መግለጫዎች ሰፊውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመመርመር ጠቃሚ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም ይህ መግለጫና ሃያ ስድስቱ አንቀጾች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምርምርና ምልከታዎች እንደ መመሪያ ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ተስፋ እናደርጋለን። የክርስቶስ ማንነትና ሥራ አስተምህሮዎች ለቤተ ክርስቲያን ማንነትና ጤና አስፈላጊ ናቸው። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ትውልድ፣ የክርስቶስን ማንነትና ሥራ ርቱዕ መረዳትን እንደ ገና ማጥናትና ማረጋገጥ አለበት። ይህ መግለጫ ይህንኑን ለማሳካት ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል እንተማመናለን።

## ለወንጌል የጋራ ዐላማ

በዓለም ዙሪያ ቍጥራቸው እየጨመረ የመጣ ቤተ እምነታዊ ያልሆኑ አብያተ ክርስቲያናት፣ ድርጅቶችና እንቅስቃሴዎች አሉ። ብዙዎቹም ወንጌልን ለማስፋፋት እያገለገሉ የሚገኙ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ጤናማ አጋርነቶችና ኅብረቶች የት ሊኖሩ እንደሚችሉ መለየት አስቸጋሪ ነው። ምናልባት ይህ መግለጫ በክርስቶስ የሆኑ ወንድሞችንና እኅቶችን ለመለየት፣ ደግሞም ለወንጌል የሚደረጉ የጋራ ጥረቶችን ለማጠናከር ሊያገለግል ይችላል።

## እንዲህ ላለው ጊዜ

በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ከተማ ውስጥ የሰማዕታት ሐውልት ይገኛል፤ ይህም እንደ ቶማስ ክራንመር፣ ኒኮላስ ሪድሊ እና ሂው ላቲመር ያሉ የብሪታንያ ተሐድሶ አራማጆች የከፈሉትን መሥዋዕትነት ያስታውሳል። የሮም ቤተ ክርስቲያን ስሕተቶችን በመቃወም፣ ያረጋገጧቸውንና የጠበቋቸውን ቅዱስ እውነቶች በመመስከር ሰውነታቸውን ለእሳት አሳልፈው እንደ ሰጡ፣ ደግሞም በክርስቶስ ማመን ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ መከራ መቀበልም ስለ ተሰጣቸው ደስ እንደ ተሰኙ ይናገራል።

የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ቅዱስ እውነቶች አመኑ፤ አረጋገጡ፤ ደግሞም ጠበቁ። ለእነዚህ እውነቶች በመመስከር፣ ዐወጇቸዋል፤ ተከላክለዋቸዋል፤ ደግሞም ስለ እነርሱ ሲሉ መከራን ተቀብለዋል። በዘመናት ውስጥ ብዙዎች እነዚህን የተሐድሶ አራማጆች ተቀላቅለዋል። በዘመናዊው ምዕራባዊ ዓለም የሚገኙት ብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት የሃይማኖት ነጻነት አግኝተው ኖረዋል። ያ ምን ያህል እንደሚቈይ አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል። ይህ ትውልድ ወይም የሚመጡት ትውልዶች በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት መከራ ለመቀበል ሊጠሩ ይችላሉ። አለመዘጋጀት ጥበብ የጐደለው ድርጊት ነው፤ የሚቀጥለውንም ትውልድ ያለ ዝግጅት መተው ጥበብ አልባ መሆን ነው።

በርግጥም፣ ስለ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ የሚናገሩት እነዚህ እውነቶች ሊታመኑ፣ ሊረጋገጡ፣ ሊጠበቁና መከራ ሊቀበሉላቸው የሚገቡ ናቸው። በክርስቶስ ሕይወት አለ።

በክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ውስጥ፣ ሕዝቡ ሁሉ እርሱን ጥለውት የሄዱበትና ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ብቻውን የቀረበት ጊዜ ነበር። እነርሱም ደግሞ ይሄዱ እንደ ሆነ ጠየቃቸው። ጴጥሮስ ለቡድኑ ተናገረ፤ “ጌታ ሆይ፥ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል አውቀናልም” (ዮሐንስ 6፥68–69)። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ጥርጣሬ ነበረው። ኢየሱስ ተሰቅሎና ተቀብሮ ነበር። ስለ ትንሣኤው ምስክርነት ነበር፤ ነገር ግን ቶማስ ተጠራጠረ። ከዚያም ኢየሱስ ለቶማስ ታየ። የክርስቶስን ቍስሎች፣ ስለ ኀጢአታችን የተቀበለውን ቍስሎች ነካ። ቶማስ፣ “ጌታዬ አምላኬም!” ብሎ መሰከረ (ዮሐንስ 20፥28)።

እንዲህ እናምናለን። እንዲህም እንመሰክራለን።